# በሕግ አምላክ

ኧረ በሕግ አምላክ ፣ ሕግ ካለ ባገር
አገር የሚመራ ፣ ሺዎች የታጠቁ ፣ እያሉት ወታደር
ባገር ላይ ተጣብቆ ፣ መንጋው እንደመዥገር
እንዴት የሰው ፍጡር ፣ በቆርቆሮ ታርዶ ፣ በድንጋይ ይወገር ?

በቋንቋ ሃይማኖት ፣ የማይመስለኝ ብሎ ፣ ሕዝብ እየተለየ
ወሮ በላ ገንኖ ፣ ዜጋ በሐገሩ ፣ እየተሰቃየ
መንግሥት ቻላ ሲለው ፣ ፊቱን ሲያዞርበት ፣ አይቶት እንዳላየ
ሕግ አለ ወይ በውነት ፣ ይህ ሁሉ ሲፈፀም ፣ ፖሊስ ቆሞ እያየ ?

እየተሰቃየ ፣ የሰላም ሰባኪ ፣ ታፍኖ ያላግባብ
ተስፋ እየቆረጠ ፣ ዜጋ ላይ ሲያጠላ ፣ ዛሬም የሞት ድባብ
ፀብን የሚዘሩ ፣ ከሕግ በላይ ሆነው ፣ ሲፏልል በጥጋብ
ሕግ ይታወቃል ወይ ፣ እንኳን የተፃፈ ፣ በገዳዮች ምናብ ?

በየ ጥጋ ጥጉ ፣ በየ ጉራንጉሩ ፣ ሁሉም ንጉሥ ፈጥሮ
እንዳሻው የሚገል ፣ ዘርፎ የሚበላ ፣ እንደ ተምቻ ወሮ
መንግሥት ተብዬው ፣ ዜጋን አይታደግ ፣ እያየ ባንክሮ
በምን መመዘኛ ፣ በምን መለኪያ ነው ፣ ሕግ አለ የሚባል ፣ ስርአት ተሸሮ ?

መንጋው በጥላቻ ፣ በንፁሃን ዜጎች ፣ መዓት ባወረደ
መለዮ ለባሹ ፣ ሰውን እንደ እንሰሳ ፣ ቆሞ ካሳረደ
የተገላቢጦሽ ፣ አራጁን አጅቦ ፣ ሟቹን ካሳደደ
ሕግ አለ ወይ ባገር ፣ ተረኛነኝ የሚል ፣ ሕጉን እየናደ ።

ግብር እየከፈለ ፣ ሰላሙ እንዲጠበቅ ፣ ከንቱ የሚማስነው
መቻ ተርፎት ሆነና ፣ እየቀነሰ ነው ፣ ልጁን ከሚያጎርሰው
ሕግ ያወጣ መንግሥት ፣ ሕግን አስከብሮ ፣ መምራት ከተሳነው
ቤተመንግሥት ገብቶ ፣ ወንበር የሚያሞቀው ፣ ስራው ግን ምንድነው ?

አሰሱን ገሰሱን ፣ ቀን ያልፋል እያለ ፣ ተሸክሞ ያዘለ
ዝንተ ዓለም አይኖርም ፣ በደልን ታቅፎ ፣ እየወነጀለ
አፀፋን ለመክፈል ፣ በቂ ብቃት አለው ፣ ጉልበቱም አልዛለ
በሕግ አንገዛም ፣ ሂሳብ ይወራረድ ፣ ይሁን ከተባለ
በዛሬ ገዳዮች ፣ ይብሳል ክፍያው ፣ እየተስተዋለ ።

በጎጥ በሃይማኖት ፣ የተደራጃችሁ
ደም ለማፍሰስ ብቻ ፣ እንቅልፍን ያጣችሁ
መታገስ ፍርሃት ፣ መስሎ አይታያችሁ
ዛሬም በሕግ አምላክ ፣ ሕግ ከገዛችሁ
ኖራችሁ ተማሩ ፣ ሞት አያስተምራችሁ ።

ታዛቢው

December 18, 2019